www.abyssinialaw.com



14ኛ ዓመት ቁጥር 6

14th Year No 6

ባህር ዳር ታህሳስ 17 ቀን 2001 ዓ.ም

Bahir Dar 26th, December 2008

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 12.86 Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ. 312 P.O.Box |



| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 64/2001 ዓ.ም<br>በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአግሮ ስቶን ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | Regulation No. 64/2008<br>The Amhara National Regional State Agro-Stone Manufacturing Enterprise Establishment, Council of Regional Government Regulation. |

## ደንብ ቁጥር 64/2001 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአግሮ ስቶን ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያን ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

## REGULATION NO. 64/2008

A COUNCIL OF REGIONL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE AGRO-STONE MANUFACTURING ENTERPRISE IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

www.abyssinialaw.com



በአገራችን ከፍተኛ እንቅስቃሴና ዕድገት እየተመዘገበባቸው ካሉት የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል የኮንስትራክሽን ዘርፍ አንዱ ስለሆነ ይህንኑ ዕድገት ለማፋጠንና በአስተማማኝ ሂደት ለማስቀጠል አስፈላጊ የሆኑ የግንባታ ማቴሪያሎች ፍላጐትና አቅርቦትን አጣጥሞ ለመሄድ የሚያስችል ሥራን ማከናወን አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፣

WHEREAS, for a construction sector is one among economic sectors having been registered great doing and growth in our country and in order to accelerate and proceed this growth in a sustainable progression, it is believed that it has been necessary to carry out an activity enabling to balance supply and demand of necessary construction materials;

በኮንስትራክሽን ዘርፍ እየታየ ያለውን የግንባታ ማቴሪያሎች የዋጋ ንረትና እጥረት ትርጉም ባለው መልኩ ለመቅረፍ ከተለመዱት የግንባታ ማቴሪያሎች በጥራት የተሻለ፣ ርካሽና ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያለው ህብረተሰብ ጭምር ሊገለገልበት በሚችል አማራጭ የግንባታ ማቴሪያል አምርቶ ማቅረብ በማስፈለጉ፣

WHEREAS, to definitely solve the problem of price hike and shortage of construction materials existing in construction sector, it has become necessary to manufacture and provide with alternative construction materials which are better in quality, cheaper in price-wise than customary construction materials and which lower and middle income community may use same thereof.

በአካባቢያችን የሚገኙ የግብርናና ሌሎች ተረፈ ምርቶችን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ሰፊ የሰው ጉልበት የሚጠቀም እና ምንም አይነት አካባቢያዊ ተፅዕኖ የሌለውን የግንባታ ማቴሪያል የማምረት ቴክኖሎጂን ማሸጋገር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ስለታመነበት፣

WHEREAS, it is believed that it has multifaceted benefit to transfer a technology of manufacturing construction material which enables to put in good use agriculture and other by-products available in our surroundings, employ massive human labour and which do not cause any environmental impact thereof;

በኮንስትራክሽን ዘርፍ ዋና የግንባታ ማቴሪያል ሆኖ የሚያገለግለውን ሲሚንቶንና የሲሚንቶ ውጤት የሆኑ ምርቶችን በሌላ አዲስ ምርት የመተካት አማራጭ እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፣

WHEREAS, it has become necessary to have an alternative of replacing cement and outputs of cement having been used as a main construction material in the construction sector with other new product.

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በተሻሻለው የክልሉ አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 120/1998 ዓ.ም አንቀጽ 34 ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

NOW, THEREFORE, the council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of art. 58, sub. Art. 7 of the Revised Regional Constitution and art. 34 of the Revised Regional State Executive Organs Re-establishment, Organization and Determination of their powers and duties Proclamation No. 120/2006, hereby issues this regulation.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአግሮ ስቶን ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 64/2001 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "አግሮ ስቶን" ማለት የግብርና ተረፈ ምርቶችንና አያያዥ፣ ጥንካሬ ሰጪ ኬሚካሎች ተቀላቅለው በተፈላጊ ቅርጽ ደርቆ ተዘጋጅቶ የሚወጣ ምርት ነው።
2. "ፋብሪካ" ማለት የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎችን በግብዓትነት በመጠቀም የማምረት ሂደትን ተጠቅሞ ወደ መጨረሻ ምርትነት በመቀየር የሚያወጣ ድርጅት/ተቋም ነው።
3. "መከፋፈያ ግድግዳ" ማለት የቤትን ወለል ውስጥ ለውስጥ የሚከፍል ግድግዳ ነው።
4. "አካባቢያዊ ተፅዕኖ የሌለው ቴክኖሎጂ" ማለት የማምረት ሂደቱ በአካባቢ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ወይም ብክለት የማያስከትል ቴክኖሎጂ ነው።
5. "ጥሬ ዕቃ" ማለት መጨረሻ ለሚወጣው ምርት በቅድሚያ የሚያገለግል ግብዓት ማለት ነው።
6. "ሰፊ የሰው ጉልበት የሚጠቀም" ማለት ለማምረት ሥራ የሰውን ጉልበት በሰፊው መጠቀም ነው።

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Agro-Stone Manufacturing Enterprise Establishment Regulation No. 64/2008."

### 2. Definition

Unless the context otherwise requires, in this regulation:

1. "Agro-Stone" means a product to be manufactured where agriculture by-products and sticky and hardening chemicals are mixed together, dried in a desired shape and prepared thereof.
2. "Factory" means an enterprise or institution which, having used various raw materials as an input and changed same into end products, manufactures outputs.
3. "Partition Wall" means a wall that divides the interior part of floor of a house.
4. "Non-Environmental Impact Technology" means a technology that does not cause any harm or pollution on the environment during production process.
5. "Raw Material" means an input used primarily for the output/end product.
6. "Using Massive Human Labour" means to largely use human labour for production activity.

www.abyssinialaw.com



7. "የማምረት ሂደት" ማለት ጥሬ ዕቃን ወደ ምርትነት ለመለወጥ የሚከናወን ሂደት ነው።

8. "መዋሃድ" ማለት የተለያየ ባህሪ ያላቸውን ግብዓቶች በአንድ ላይ መገናኘት ነው።

9. "ምርት" ማለት የምርት ሂደቱን አጠናቆ በመጨረሻ የሚገኝ ውጤት ነው።

10. "ማሽን" ማለት የማምረት ሂደትን ለማከናወን የሚያገለግል መሳሪያ ነው።

11. "የቁመት ጊዜ" ማለት የማምረት ሂደት ተቋርጦ የቆየበት ጊዜ ነው።

12. "ተከላ" ማለት ለማምረት ሂደት የሚያገለግል ማሽኖችንና መሳሪያዎችን አገልግሎት ሊሰጡ በሚችሉበት ቦታ ላይ ማስቀመጥ ነው።

13. "የማሽን ፍተሻ" ማለት ለማምረት ሂደት የሚያገለግሉ ማሽኖችና መሳሪያዎች የማምረት ሥራ ከመጀመራቸው በፊት መስራታቸውን ማረጋገጥ ነው።

14. "የባለቤትነት መብት" ማለት በህጋዊ አካል የተሰጠና ከባለመብቱ ፈቃድ ውጭ ማንም ሊጠቀምበት የማይችል መብት ነው።

7. "Production Process" means a process to be undertaken to change raw material into product.

8. "Compound" means to mix inputs having several characteristics, together to form a single thing.

9. "Product" means an output obtained through completing its production process.

10. "Machine" means a device served to carry out production process.

11. "Down-Time" means a period of time in which the production is interrupted thereof.

12. "Machine-Erecting" means to fix machines and tools used for production process at a place where they serve thereof.

13. "Machine-Commissioning" means to check machines and tools used for production process that they are whether or not operational, before they launch production.

14. "Patent" means a right given to a person by legal body and used by no one else without prior permission of the owner himself.

www.abyssinialaw.com



# ክፍል ሁለት

## ስለ አግሮስቶን ማምረቻ ድርጅት መቋቋም ዓላማ፣ ሥልጣን፣ ተግባርና ድርጅታዊ አቋም

### 3. መቋቋምና ተሪጠነት

1. የአማራ ክልላዊ መንግስት አግሮስቶን ማምረቻ ድርጅት /ከዚህ በኋላ "ድርጅት"/ እየተባለ የሚጠራ ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት ፋብሪካ ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የድርጅቱ ተጠሪነት ለክልሉ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ይሆናል። ፕሮጀክት ጽ/ቤቱም ሥራውን ሊያስተባብር የሚችል አየረጃጀት ሊፈጥር ይችላል።

### 4. ዓላማ

ድርጅቱ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. መከፋፈያ ግድግዳዎችን ማምረት፣
2. ቀላል፣ ርካሽ እና በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ የሌላቸው ለግንባታ የሚውሉ ግብዓቶችን ማምረት፣
3. ሲሚንቶ፣ ኮንክሪት ብሎኬቶችን፣

# PART TWO

## ESTABLISHMENT, OBJECTIVE, POWERS AND DUTIES AND ORGANIZATIONAL STRUCTURE OF THE AGRO-STONE MANUFACTURING ENTERPRISE

### 3. Establishment and Accountability

1. The Amhara National Regional State Agro-stone manufacturing Enterprise (hereinafter referred to as "the Enterprise"), is hereby established under this regulation as an autonomous enterprise of the regional state having its own legal personality.
2. The accountability of the Enterprise shall be to the Regional Houses Development Project Office. And the Project Office may create an organization which enables itself to coordinate and facilitate the activity.

### 4. Objective

The Enterprise shall, pursuant to this regulation, have the following objectives

1. To manufacture wall dividers;
2. To manufacture construction inputs which are simple, cheap and do not have impact on the environment;
3. To substitute cement, concrete-blocks,

www.abyssinialaw.com



የቆርቆሮ ጣራዎችን እና በሮችን በሌላ አማራጭ ምርት መተካት፣

corrugated sheets of roofs and iron doors with other options.

4. በቀላሉ የሚገጠሙ፣ ክብደታቸው ቀላል የሆነ፣ ምንም ዓይነት ተጨማሪ የልስን ሥራ የማይጠይቁ እንዲሁም በውሃ የማይበላሹ፣ መንቀጥቀጥንና የእሳት አደጋን መቋቋም የሚችሉ እና ድምፅ የማያስተላልፉ መከፋፈያ ግድግዳዎች ማምረት፣

4. To manufacture partition walls which are easily installable, light in their weight, needs no extra smoothing activity as well as not spoiled with water, resistible to shock and fire-hazard and do not transmit sound through.

5. ለግሉ ኢንቨስትመንት አዲስ የግንባታ ግብዓት አመራረት ቴክኖሎጂን ማለማመድ፣

5. To adapt a technology of manufacturing new construction inputs to private investment;

6. በአካባቢ ሊገኙ ከሚችሉ የተለያዩ ግብዓቶች ለግንባታ የሚውሉ ምርቶችን የማምረት ሂደት ላይ ቀጣይ የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፣

6. To carry out sustainable research activities on process of manufacturing products, from various inputs may available in the surrounding, used for construction purpose.

## 5. የድርጅቱ አድራሻ

የድርጅቱ መደበኛ አድራሻ ደሴ እና ባህር ዳር ከተሞች ሆኖ ወደፊት እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች የሚቋቋም ይሆናል።

## 5. Principal Address of the Enterprise

The principal address of the enterprise shall be in Dessie and Bahir Dar. As deemed necessary, it shall be established at any other places.

## 6. ድርጅታዊ አወቃቀር

ድርጅቱ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

1. የሥራ አመራር ቦርድ፣
2. የምርትና ቴክኒክ ሥራ አስኪያጅ፣
3. የተለያዩ ክፍሎች ኃላፊዎች፣
4. ሌሎች ባለሙያዎች፣ እንደአስፈላጊነቱ በማህበር የተደራጁ ባለሙያዎች፣ ደጋፊ እና የጉልበት ሠራተኞች።

## 6. Organizational Structure

The enterprise shall, pursuant to this regulation, have the following bodies:

1. A managing board;
2. A manager of product and technique;
3. Heads of various divisions ;
4. Other professionals, as deemed necessary, professionals organized in association, support employees and laborers;

www.abyssinialaw.com



## 7. የሥራ አመራር ቦርድ ስለመቋቋም

1. የድርጅቱን የማምረት ሥራ የሚከታተልና ድጋፍ በማድረግ የሚመራ ጉዳዩ የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች በአባልነት የሚኖሩበት የድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ ከዚህ በኋላ /"የሥራ አመራር ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ/ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

## 8. ስለ ድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ አሰያየም እና የአባላት ጥንቅር

1. ድርጅቱ በክልል ደረጃ የሚቋቋም የሥራ አመራር ቦርድ ይኖረዋል።
2. የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ ር/መስተዳድር ይሆናል።
3. ቦርዱ ከዚህ በታች የተመለከቱት አባላት ይኖሩታል፦
   1) የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊ ……………………………..…… ሰብሳቢ
   2) የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ……………………………..…..... አባል
   3) የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ ……………………………….. አባል
   4) የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ኃላፊ ……………………………….. አባል
   5) የገጠር ኢነርጂና ማዕድን ሃብት ልማት ማስ/ኤጀ/ ሥራአስኪያጅ …………. አባል
   6)
   7) የክልሉ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ………………….. አባል
   8) የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ ኃላፊ ……………………………..…... አባል
   9) የአካ/ጥበቃና መሬት አስተ/ባለሥልጣን

## 7. Establishment of a Managing Board

1. Board oft he Enterprise /hereinafter referred to as "A Managing Board"/, having memberships form concerned government offices, that follows up manufacturing activity of the enterprise and manage same by supporting thereof.

## 8. Designation and Composition of Members of Managing Board of the Enterprise

1. The enterprise shall have a managing board established at the regional level.
2. Accountability of the board shall be to the Head of the Regional Government.
3. The board hall have the following bodies:

1. A Head of Works and Urban Development Bureau ………………….……. Chair Person
2. A Head of Finance and Economic Development Bureau …………………………. member
3. A Head of Trade and Industry Bureau ……………..…………… member
4. A Head of Agriculture and Rural Development Bureau ………….. member
5. A Manager of Rural Energy and Mine Resource Development Promotion Agency ……………………..…… member
6. A Manager of the Regional Houses Development Project Office …….. member
7. A Head of Water Resource Development Bureau …………………………. member
8. A Manager of Environment Protection and Land

www.abyssinialaw.com



ሥራ አስኪያጅ ……………..…….. አባል

10) የድርጅቱ የምርት ቴክኒክ ሥራ አስኪያጅ…………………..…. አባልና ፀሐፊ

## 9. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ቦርዱ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የድርጅቱን ስትራቲጂካዊ ዕቅድ ይነድፋል፣
2. የድርጅቱን ዕቅድ መርምሮ ያፀድቃል፣ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያዳምጣል፣ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፣ መመሪያዎችን ይሰጣል፣
3. የታቀዱ ተግባራት በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ ወይም ፕሮግራም መሠረት እየተፈፀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ክትትልና ግምገማዎችን ያካሂዳል፣
4. ለድርጅቱ የሚያስፈልገውን በጀት ረቂቅ በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ ለክልሉ መንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አጠቃቀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
5. የድርጅቱን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በሚያስችሉ ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ውሣኔዎችን ያሳልፋል።

## 10. የድርጅቱ ሥልጣንና ተግባር

ድርጅቱ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1) መከፋፈያ ግድግዳዎችን በሚፈለገው ዓይነትና ብዛት በተቀዳሚነት ለክልሉ

Administration Authority ………. member

9. A Manager of Product and Technique of the Enterprise ……..……. member and secretary

## 9. Powers and Duties of the Board

The Managing Board shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. Devise strategic plan of the enterprise;
2. Examine and approve plan of the enterprise, consider timely reports, show directions and give directives;
3. Carry out follow-up and evaluations enabling it to ascertain that planned activities are implemented on the basis of the time-table or program scheduled thereof;
4. Look into budget draft necessary for the enterprise and submit same to the Regional Government and cause its implementation upon approval; follow up and supervise over its management;
5. Discuss upon such other related issues which enables the attainment of objectives of the enterprise and pass decision;

## 10. Powers and Duties of the Enterprise

The Enterprise shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties;

1. Manufacture partition walls in a desired type and quantity primarily to the Regional Houses Development Project

www.abyssinialaw.com



ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት እንደ አስፈላጊነቱ የተጠቃሚዎችን ፍላጐት መሠረት በማድረግ ያመርታል፣

2) የሠራተኞችን ደህንነትና አካባቢያዊ ብክለትን የማያስከትል የማምረት ሥርዓትን ይከታተላል፣

3) የምርት ጥራትን ለማሻሻል የምርምር ሥራን በስፋት ያከናውናል፣

4) የአመራረት ሂደትን በየጊዜው በመፈተሽ ምርቱ በገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ የሚቀጥልበትን ሥራ አጠናክሮ ይሠራል።

5) በየጊዜው የሠራተኞችን የማምረት አቅም የሚያጐለብት ሥልጠና ይሰጣል፣

6) የነፃ ገበያ መርህን በመጠበቅና የኢንዱስትሪ ሠላምን በማስፈን ይሠራል፣

7) የጥራት ሥራ አመራር ሥርዓትን በመከተል ይሠራል፣

8) ለሥራ አመራር ቦርድ ስለ ፋብሪካው አጠቃላይ የማምረት እንቅስቃሴ በየጊዜው ሪፖርት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣

9) ተጨማሪ የተለያዩ ምርቶችን ያመርታል፣

10) ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር የተለያዩ ድርጅቶች ጋር የሥራ ግንኙነት ይፈጥራል፣

11) የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ በህግ መሠረት ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

12) ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፣

Office and as deemed necessary on the basis of the beneficiaries, to others.

2. follow a product-system which does not cause environmental pollution and maintain security of employees.

3. extensively carry out research activity in order to improve quality of product,

4. Inspect process of producing form time to time and undertake the activity that the product to remain competitive in market.

5. Provide, form time to time, a training that enhances producing capacity of the employees;

6. Work its activity in a manner of maintaining principle of free-market and prevailing industrial tranquility thereof.

7. work following a system of quality managements;

8. Prepare and submit to the managing board timely reports concerning overall production activity of the factory;

9. Manufacture additional various products;

10. create working relationship with foreign and domestic various enterprises having similar objective;

11. own property, enter into contract, as well as sue and be sued in its own name in accordance with law;

12. Perform such other functions as may be helpful to accomplish its objectives.

www.abyssinialaw.com



# ክፍል ሦስት
# ስለ ሥራ አስኪያጅ አሰያየም፣ ተጠሪነትና ሥልጣን

## 11. የሥራ አስኪያጅ አሿሿም

1) ሥራ አስኪያጅ በክልሉ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾም ይሆናል።

2) የሥራ አስኪያጁ ተጠሪነት ለክልሉ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ይሆናል።

## 12. የሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 ሥር ለድርጅቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት የማስፈፀም ኃላፊነት ሲኖረው በተጨማሪም የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1) የድርጅቱን አጠቃላይ ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣

2) የድርጅቱ የሥራ ዕቅድ፣ የማምረት ፕሮግራምና በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ያስወስናል።

3) በድርጅቱ ስም የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ይህንኑ የሚያንቀሳቅሱ ሰዎችን ይሰይማል፣ ሂሣቡ በትክክል መያዙን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፣

4) ለድርጅቱ የማምረት ሂደት ቅልጥፍና

# PART THREE
# DESIGNATION, ACCOUNTABILITY AND POWERS OF THE MANAGER

## 11. Appointment of the Manager

1. The manager shall be appointed by the head of the Regional Government upon his representation by the Regional Houses Development Project office.
2. The manager shall be accountable to the Regional Houses Development Project Office.

## 12. Powers and Duties of the Manager

The manager of the enterprise shall have powers and duties vested to the enterprise under art. 10 of this regulation hereof as well as the following powers and duties.

1. Manage, administer and supervise over overall activities of the enterprise;
2. Prepare, submit and cause its approval work plan, production programme and budget proposal;
3. Open bank account in the name of the enterprise, designated persons who operate this; supervise over and ensure that the account shall be kept accurately;
4. be able to delegate part or all of his

www.abyssinialaw.com



በሚያስፈልገው መጠን ሥልጣንና ተግባራቱን በከፊል ወይም በሙሉ ለበታች የሥራ ኃላፊዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፣

5) ድርጅቱን በመወከል በሕግ መሠረት ውሎችን ይዋዋላል፣

6) የድርጅቱን እንቅስቃሴ በየወቅቱ ለሚመለከባቸው አካላት ሪፖርት ያቀርባል፣

7) የድርጅቱን የሰው ሃይል ይቀጥራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ ያሰናብታል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 13. ስለ በጀት

የድርጅቱ የበጀት ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1) በክልሉ መንግስት የሚመደብ በጀት፣

2) የውስጥ ገቢ፣

3) ሌሎች ምንጮች

### 14. የሂሣብ መዛግብትና እና ኦዲት

1) ድርጅቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፣

2) በሂሣብ መዛግብቱና በገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች አያያዝና አጠባበቅ ረገድ ድርጅቱ ተቀባይነት ያላቸውን የአሠራር መርሆች ይከተላል፣

3) የድርጅቱን የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብም

powers and duties to the subordinate heads to the extent necessary for the effectiveness of production process of the enterprise;

5. representing the enterprise, enter into contracts in accordance with law;

6. periodically submit to the concerned bodies report concerning activities of the enterprise;

7. Recruit employ, direct, supervise over and dismiss human power of the enterprise.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 13. Budget

The source of the budget of the enterprise shall be the following:

1. budget to be allocated by the Regional Government;
2. Internal income;
3. Other resources

### 14. Books of Account and Auditing

1. The enterprise shall keep books of account which are accurate and complete thereof;
2. the enterprise shall pursue legal working principles with regard to keeping and maintenance of books of account and financial as well as property related documents of the enterprise.
3. the books of account and financial as well as property related documents of the

www.abyssinialaw.com



ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች በየጊዜው ያስመረምራል፣

## 15. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ፋብሪካው ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜና ሁኔታ የመተባበር ግዴታ አለበት።

## 16. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጐች

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ የተሸፈኑትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፣

## 17. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

የሥራ አመራር ቦርዱ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚረዱ ዝርዝር መመሪያዎችን የማውጣትና በተግባር ላይ እንዲውሉ የማድረግ ሥልጣን አለው።

## 18. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ታህሳስ 17 ቀን 2001 ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር

enterprise shall be audited form time to time by Internal and External Auditors.

## 15. Obligation to Co-operate

Any natural person or organ having given personality right by law shall have an obligation to cooperate with the office while performing its activity and conditions thereto.

## 16. Inapplicable Laws

Any other regulation, directive or customary practice shall not apply to matters concerned in this regulation provided therein.

## 17. Power to Issue Directive

The managing board shall have the power to issue specific directives may be helpful for the implementation of this regulation.

## 18. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar

This 26th Day of December, 2008

Ayalew Gobezie

Head of Government of Amhara

National Regional State